ስምዖን ዘዓምድ

/ጌታቸው በቀለ/

ቅድስት ቤተ ክርስቲያን ቅዱሳንን በብቃታቸው፣ በሃይማኖት ጽናታቸው፣ በሐዋርያዊ ተልእኳአቸውና በተአምር ሠሪነታቸው የቅዱስነት ደረጃ እየሰጠቻቸው በስማቸው ታቦት ቀርጸ፣ ገድላቸውን ጽፋ ታከብራቸዋለች።

ቅዱሳን በመራራ ተጋድሎና መሥዋዕትነት በሐዋርያዊ ተልእኮ ስብከተ ወንጌልን በማስፋፋት ተግባር ላይ የሚሠማሩት የዕለት ምግብ፣ የዓመት ልብስ አጥተው፣ ተጋድሎን እንደ አንድ መተዳደሪያ አማራጭ በመውሰድ አይደለም። ከነገሥታት ተወልደው፣ በቤተ መንግሥት አድገው፣ የዚህን ዓለም ምቾትና ቅንጦት ተድላና ደስታ ንቀው በመተው በክርስቶስ ትምህርተ ወንጌል ተመሥጠው እንደ አባቶቻቸው ሐዋርያት፣ ጻድቃንና ሰማዕታት ዘለዓለማዊውን ሕይወት በመምረጥ ወደ ፍጹም ምናኔና ገድል የገቡ ናቸው። ከእነዚህ ቅዱሳን መካከል አንዱ ስምዖን ዘዓምድ ነው።



በአምስተኛው ምእተ ዓመት አዲስና ዓይነተኛ የቅድስና መንገድ፣ አዕማድ ለተባሉ ቅዱሳን አባት በሆነው በስምዖን ተከፈተ። እነዚህ ቅዱሳን ለረጅም ዓመታት፣ እግዚአብሔርን በመሻት ቀንና ሌሊት፣ በጋና ክረምት፣ ዝናምና ፀሐይ፣ ውርጭና ንዳድ እየተፈራረቀባቸው በተራራ ላይ፣ ጣራ በሌለው ቤት በጾምና በንስሐ በተጋድሎ አሳልፈዋል። በዚሁ ተጋድሎአቸው ሊያልፉበት ጭንቅ የሆነውን ጠባቡን የገነት መንገድ አለፉ።

የስምዖን ታሪክ በዘመኑ ከነበሩ እና የዐይን ምስክር ከሚሆኑ ሦስት ሰዎች የተገኘ ነው። የእንጦንስ፣ ቆዝሞስ እና በተለይ ደግሞ በዝርዝር የጻፈው ቴዎድሮት ይጠቀሳሉ። ቴዎድሮት ታሪኩን «የጻፈለት» ስምዖን ከማረፉ ከ16 ዓመታት በፊት ነበር።

ቅዱስ ስምዖን የተወለደው በ389 በሲሳ /Sissa/ ከተማ ነው። ከተማዋ ከቂሮስ በስተ ሰሜን ምዕራብ አቅጣጫ 40ኪ.ሜ ርቀት ላይ ትገኛለች። ስምዖን የሚናገረው ቋንቋ አርመን ሲሆን በኋላ የግሪክ ቋንቋ በገዳሙ ውስጥ ተምሯል። /History of the Christian Church, Volume III: Nicene and post- Nicene Christianity,A.D.311 – 600/

በነሐሴ 3 ቀን የሚነበበው ስንክሳር እንደ ሚተርከው ስምዖን ዘዓምድ በተወለደ በስድስት ዓመቱ እንደ አገራቸው ልማድ በሶርያ እና በኪልቂያ ድንበር ላይ በምትገኝ ቦታ የአባቱን በጐች ይጠብቅ ነበር። ስምዖን በአባቱ የታዘዘውን የእረኝነት ተግባሩን እየተወጣ የ13 ዓመት ብላቴና ሳለ ፍቅረ እግዚአብሔር በልቡ አድሯልና ወደ ቤተ ክርስቲያን እየሄደ ቅዱሳት መጻሕፍትን ይሰማ ነበር። በልቡናው ዘወትር እግዚአብሔርን ያስብ ቸርነቱንም ያደንቅ ነበር። በኋላም በቤተ ክርስቲያን ሲነበብ ይሰማው እና ይመኘው በነበረው በቅዱሳን ሕይወት ተማርኳልና ራሱን ለገዳማዊ ሕይወት አዘጋጀ።

ስምዖን የእግዚአብሔር ቸርነት አነሣስቶት፤ በሰማው ቃለ እግዚአብሔር ልቡናው ተሰብሮ በዓለም ከመኖር ይልቅ እንደ ቅዱሳን አባቶቹ በበረሓ ወድቆ እግዚአብሔርን ማገልገል የሚሻል መሆኑን ተገነዘበ።

አብርሃም ከእግዚአብሔር ጋር ለመገናኘት ከወገኑ ከቤተሰቡ ተለይቶ እንደ ወጣ፣ በሐዲስ ኪዳንም መጥምቀ መለኮት ቅዱስ ዮሐንስ ለሠላሳ ዓመታት ያህል በበረሓ እንደ ኖረ ስምዖን ዘዓምድም ይመኘው የነበረውን የክርስትና ሕይወት በመሻት በከተማው አቅራቢያ በምትገኝ ወደ አንዲት አነስተኛ ገዳም ሄደ። ወደ ገዳሙም በደረሰ ጊዜ ሳይበላና ሳይጠጣ ገዳማውያኑ ሊያዩት በሚችሉት በገዳሙ መግቢያ ፊት ለፊት ወደቀ። ገዳማውያኑም እንደ አንድ ትንሽ አገልጋይ ተቀብለው ወደ ገዳሙ ያስገቡት ዘንድ ተማፀናቸው።

«ጸጋ ክብር ለማግኘት ምግባር ትሩፋትን አብዝቶ ለመሥራት የሚወድ ሰው ቢኖር አስቀድሞ ከዓለማዊ ግብር መለየት ይገባዋል» እንዳለ ቅዱስ ይሥሐቅ በመጽሐፈ መነኮሳት በዚህ ዓለም ለጊዜው ሰውነትን ደስ ከሚያሰኘው ነገር መከራ መቀበልን ነው ስምዖን የመረጠው።

ስምዖን በዚያ ገዳም በፍጹም ትሕትና ወደ ገዳሙ አበ ምኔት ቀርቦ ይመኘው የነበረውን የክርስትና ሕይወት ነግሮ ወደ ገዳሙ እንዲያስገቡት ተማፀናቸው። አበ ምኔቱ ስምዖንን የገዳሙ አባል አድርገው ከመቀበላቸው በፊት ልጅነቱን ተመልክተው ከባድና አስቸጋሪ የሆነውን የምንኩስና ሕይወት ሊቋቋም እንደ ማይችል

ቢነግሩትም ስምዖን ግን አልተቀበለውም፤ በፈቃደ እግዚአብሔር ነበርና የተጓዘው በገዳሙ እያገለገለ መነኮሰ። ለብዙ ዘመናትም በገድል ተጠምዶ በጾም፣ በጸሎት፣ በስግደት ተወስኖ ኖረ።

ስምዖን በሳምንት አንድ ቀን በዕለተ እሑድ ብቻ መመገብን አስለመደ፤ በጾም ወቅት አርባውን ቀናት በሙሉ በመጾም ያለምግብ ይሰነብት ነበር። ይህን መሰል ሕይወት በሞቃታማው የአየር ጠባይ እንኳን በጣም የማይታመን ነው። ይህን መሰሉ የመንፈሳዊ ሕይወት ተጋድሎ እስከ ሞት አድርሶት ነበር። ነገር ግን የነበረው የመንፈሳዊ ሕይወት ጥንካሬ የደረሰበትን መከራ አስቻለው። ቴዎዶሬት ሲጨበኘው ዐቢይ ጾምን ያለምንም እህል ውኃ አሳልፎ ነበር። በዚህም ነቢያቱን ሙሴን፣ ኤልያስንና ፈጣሪው ኢየሱስ ክርስቶስን መስሏቸዋል።

/History of the Christian Church, volume III: Nicene and post-Nicene Christianity. A.D. 311-6001. /

ሌላውና ስምዖን ዘዓምድን ከሌሎች ቅዱሳን ለየት የሚያደርገው ተጋድሎ ደግሞ ሰውነቱን ቀጭንና ጥልፍልፍ ባለ ገመድ አጥብቆ ማሰሩ ነው። ስምዖን ዘዓምድ ወገቡን የታጠቀበት ገመድ ሥጋውን /ሰውነቱን/ ከርክሮ ቆርጦት እስከ አጥንቱ ይደርስ ነበር። ወገቡን የታጠቀበት ገመድ ሰውነቱን ከርክሮ ስለ ቆረጠው ሰውነቱ ቆሰለ፣ ተላ፣ ከሰውነቱ የሚከረፋ ሽታ ይወጣ ነበር። ይህም አሠቃቂ የሆነ ሕማም አድርሶበታል። ከመሸተቱ የተነሳ በአጠገቡ ሰው አያልፍም፤ የሚጠጋውም አልነበረም። በዚህ ክፉ ጠረን በዚያ ገዳም የሚኖሩ መነኮሳት ተጸየፉት፤ በዐይናቸው ሊያዩትም አልወደዱም። ስንክሳሩ እንደ ሚተርከው መነኮሳቱ ወደ አበ ምኔቱ ተሰብስበው በመሄድ «ይህን መነኰስ ስምዖንን ከዚህ ገዳም አባርርልን፣ አንፈለገውም፤ በእርሱ የሚገኘው ጽድቅ ይቅርብን፤ ከሰውነቱ የሚወጣው ሽታ አላስቀመጠንም፤ የማታባርርልን ከሆነ ግን ገዳሙንም አንተንም ጥለን እንሰደዳለን» ብለው። ለመኑት// /ስንክሳር ዘወርኀ ነሐሴ/።

አበ ምኔቱ የሰማው ነገር ሁሉ አዲስ ሆነበት። በመነኮሳቱ አባባል ተገርሞ፤ «ምንድን ነው ጥፋቱ? እስቲ ችግሩን በዝርዝር አስረዱኝ? ለምን በሰው ትፈርዳላችሁ?» አላቸው። እነርሱም «ነግረንሃል፡ በተጨማሪም ማየት ማመን ነውና አንተ ራስህ መጥተህ እይና ለችግራችን መፍትሔ ስጠን?» አሉት።

አበ ምኔቱ የመነኮሳቱን ቃል ሰምቶ ስምዖንን አስጠርቶ አንድ ጥያቄ ጠየቀው፤ ስምዖንም መጥቶ በፊታቸው ቆመ። ከተጋድሎው የተነሣ ከሰውነቱ ደምና መግል በእግሮቹ ላይ ይፈስ ነበር። አበ ምኔቱም ስምዖን ዘዓምድን ተመልክቶ እጅግ ተጨነቀ። የስምዖንን ልብስ ገልጦ ሲመለከት ሰውነቱን ከርክሮ የገባውን ገመድ አይቶ አዘነ። ስምዖንን፡ጠ «ሰውነትህ እንደዚህ እስኪቆስል ድረስ ይህን ታደርግ ዘንድ እንዴት ደፈርክ?» አለው። ሰውነቱን ከርክሮ የገባውን ገመድ ቀስ ብሎ አወጣለት። ቁስሉም እስከ ሚድንለት ድረስ ለጎምሳ ቀናት ያህል መድኃኒት አደረገለት።

በኋላም አበ ምኔቱ በገዳሙ ያሉ ሌሎች መነኮሳትን በመፍራቱ ስምዖንን እንዲህ አለው፡- «ልጄ ስምዖን ሆይ ከእንግዲህ ከዚህ ገዳም መቆየት አትችልም። መነኮሳቱ ይልቀቅልን ስላሉ ገዳሙን ለቅቀህ እግዚአብሔር ወዳዘጋጀልህ ሥፍራ ሂድ» አለው። ስምዖን ግን ያልተለመደና እንግዳ ነገር ሆነበት። በዚህም ምክንያት ከገዳሙ ተባረረ። የታሪክ ባለሞያው ዶ/ር ሥርግው ሐብለ ሥላሴ ነሐሴ ሦስት ቀን የሚነበበውን ስንክሳር መሠረት አድርገው የአማርኛ የቤተ ክርስቲያን መዝገበ ቃላት በተሰኘ መጽሐፋቸው እንዳሰፈሩት፡- «እውነተኛና ታማኝ የሆነው ታሪክ ጸሐፊ የቂሮሱ ቴዎድሮስ ስለ ሶርያው ቅዱስ አባት ቴሌሣ በሚባለው ገዳም ውስጥ ኑሮውን ጀምሯል። ይህ ቅዱስ አባት ወጣት የሶርያ መነኩሴ ሰውነቱን በገመድ አጥብቆ ስላሰረው ሥጋው እንዲቆራረጥ፣ እንዲቆስልና እንዲመግል ከማድረጉም በላይ ከፉቅ የሚሸትና የሚከረፋ ሆኗል። በዚህም የተነሣ በገዳሙ አብረውት የሚኖሩት መነኮሳት «ሽተተን፣ ከረፋን» ብለው ለገዳሙ አበምኔት በመክሰስ ከገዳሙ እንዲባረር አድርገዋል።» በማለት ዘግበውታል።

ስምዖን ዘዓምድ አልከፋውም፤ ገዳማችንን ይልቀቅልን ባሉት መነኮሳትም አላዘነባቸውም። ሰውነቴ ቆስሎ፣ ደምና መግል እየፈሰሰኝ ወንድሞቼ መነኮሳት አባረውኝ ማን ያስጠጋኛል? ወዴትስ እሄዳለሁ? አላለም። እግዚአብሔርን ተስፋ አድርጌ በተጋድሎው ጸንቷልና ገዳሙን ለቆ እግዚአብሔር ወደ አመለከተው ቦታ ተጓዘ። ስምዖንን በገዳሙ ያሉ መነኮሳት ጠልተው ቢያባርሩትም፤ እግዚአብሔር ለስምዖን ተከባክበው የሚቀበሉትን አራዊት አዘጋጀለት። ስምዖን እባቦችና ጊንጦች በሚኖሩበት ጉድጓድ ውስጥ ሔዶ ገባ። እባቡም ጊንጡም አልነደፉትም። ከእነርሱ ጋር በሰላም ጸሎቱን እያደረሰ እግዚአብሔርን እያመሰገነ ኖረ።

የገዳም አበ ምኔት ራእይ አየ፤ በራእዩም፡ጠ «አገልጋዬ ስምዖንን ለምን ሰደድከው፤ አሁንም ፈልገህ መልሰው፤ በፍርድ ቀን እርሱ ከአንተ ይሻላልና» ብሎ እግዚአብሔር ገሠጸው።

በነጋም ጊዜ አበ ምኔቱ ራእይ እንዳየ ስለ አባ ስምዖንም እግዚአብሔር እንደ ገሠጸው ለመነኮሳቱ ነገራቸው። ወንድሞቹ መነኮሳቱም ደነገጡ፤ እጅግ አዘኑ፤ ወዴት ሄደን እንፈልገው?» አሉ። አበ ምኔቱም፡ጠ «ይገኛል በምትሉት ቦታ ፈልጉት። እግዚአብሔርም ያለበትን ቦታ ያመለክታችኋል» አላቸው። መነኮሳቱም ሄደው ፈለጉት፤ ግን አላገኙትም። በድጋሚ መብራት እያበሩ ለፍለጋ ሄዱ፤ ስምዖን በሚኖርበት በአንድ ጉድጓድ አጠገብ ደረሱ። ወደ ጉድጓዱ ሲገቡ ያለ መብልና መጠጥ ከእባቦችና ከጊንጦች ጋር ተቀምጦ አዩት።

ከጉድጓዱ አወጡት። ሰውነቱ ቆስሎ ይሸታል፤ ከዚህ ገዳም ይውጣልን ብለው የአባረሩት መነኮሳት በፊቱ መቆም አልተቻላቸውም። በአደረጉት ሥራ ተጸጽተው፣ አዝነው በፊቱ ሰገዱ። «በአንተ ላይ ያደረግነውን

በደላችንን ይቅር በለን፤» አሉት። ስምዖንም «እኔም አሳዝኛችኋለሁ፤ ይቅር በሉኝ» አላቸው። ከዚህም በኋላ ወደ ገዳማቸው ወሰዱት። በብዙ ገድልም ተጠምዶ፣ ጸሎት እያደረገ፣ ሕመማንን እየፈወሰ ምእመናንን እያስተማረ ሲያገለግል ኖረ።

በኋላም በ416 ዓ.ም ስምዖን ከዚያ ገዳም በሥውር ወጥቶ ወደ አንዲት /ዐለት/ ቋጥኝ ሄደ። ኑሮውንም በዚያ የሊሎን ተራራ /ምጸጭነተ ልፀለጸጸነ/ አደረገ። በኋላም ተራራው በቅዱስ ስምዖን ስም ተሰይሞ የቅዱስ ስምዖን ተራራ ተብሏል። በእርሷም ላይ ሳያርፍና ሳይተኛ በገድል ተጠምዶ ስድሳ ቀን ቆመ። ነሐሴ ሦስት ቀን የሚነበበው ስንክሳር እንደ ሚተርከው፦ ለስምዖን የእግዚአብሔር መልአክ ስለ ብዙ ሰዎች ድኅነት እግዚአብሔር እንደ ጠራው ነገረው። ከዚያም ቦታ ሔዶ ቁመቱ ሠላሳ ክንድ የሚሆን የድንጋይ ምሰሶ አግኝቶ፣ በዚያ ላይ ሁኖ፣ ድንቅ ተአምራትን እያደረገ፣ በሽተኞችንና ድውያንን እየፈወሰ፣ ወደርሱ የሚመጡትን ወንጌል እያስተማረ፣ የእግዚአብሔር ወዳጆች እያደረገ ዐሥራ ሁለት ዓመት በድንጋይ ምሰሦው ላይ ቆመ። በዚህም /ስምዖን ዘዓምድ/ የሚል ስያሜ አገኘ። ስምዖን የነበረበትን ምሰሶ /ዓምድ/ አሠራርና በምሰሶው /በዓምዱ/ ላይ የቆየበትን ጊዜ በተመለከተ ታሪክ ጸሐፊው እንደሚከተለው አስፍሯል።

እርሱ ራሱ ያቆመውና ለአራት ዓመታት ያህል የኖረበት የመጀመሪያው ዓምድ ስድስት ጫማ ከፍታ ነበረው። ሁለተኛው፡ጠ ዐሥራ ሁለት፣ ሦስተኛው ሃያ ሁለት፣ አራተኛው፡ጠ ሰዎች ለእርሱ ያቆሙለት እና ለሃያ ዓመታት በቁመት ያሳለፈበት ዓምድ ደግሞ እንደ ቴዎዶር አባባል 36 እንደ ሌሎቹ ደግሞ አርባ ጫማ ከፍታ ነበረው። የዓምዱ ጫፍ ስፋትም ሦስት ጫማ ነበር። በጫፉ ላይ ትንሽ ርብራብ ሲኖር ዐረፍ የሚለውም እዚያ ነበር። ደቀ መዛሙርቱ በመሰላል እየወጡ ምግብ ያቀብሉት ነበር።

ቴዎዶር /Theodore/ ወደ ስምዖን በርካታ ሕዝብ ይጐርፍ እንደ ነበር እንዲህ በማለት ተርኳል፦ «በ444 ዓ.ም ስምዖን ዘዓምድን የጐበኘ አንድ የታሪክ ጸሐፊ ስምዖን በአካባቢው ዝናው የተሰማ ሰው እንደ ነበርና እርሱን ለማየትና ከእርሱም በረከትና ምክር ለመቀበል ብዙ ሰዎች ይጐርፉ እንደ ነበር ጽፏል። ስምዖን ግን ይህን ዝና እና የሰው ብዛት አያስደስተውም ነበር። ለዚያ ክብር እንደተገባ አድርጎ አይቆጥረውም። ሰዎች እንዲያ እንዲያደርጉም አይመክራቸውም ነበር። እርሱን ለመጐብኘት ከሁሉም የዓለም መዓዘናት ይመጡ ነበር። ፋርሶች፣ አርመኖር፣ ኢቤሪያንስ፣ ፣አርመኖች፣ ጋሊዮስ፣ ስፔኖች፣ ብሪቴኖች... /History of the Christian Church, Volume III: Nicene and Post - Nicene Christianity. A.D.311-600/.

ቅዱስ ስምዖን በቀን ሁለት ጊዜ ለሕዝቡ ካስተማረ በኋላ ምክር ይሰጥና በሽታ ያለባቸውን በጸሎቱ ይፈውሳቸው ነበር። የእምነት ክርክሮችና ውዝግቦች በሚፈጠሩበት ሰዓት እየረገበ መፍትሔ እየሰጠ፣ የኦርቶዶክስን እምነት እያስፋፋ፣ ወንጌልን እያስተማረ፣ ነገሥታቱን እየገሠጸ፣ ኢ- አማንያንን ወደ ክርስትና መልሷቸዋል። ስምዖን መልካም ሐዋርያ ነበር።

ሁለት ሜትር ስፋት ባለው የምሰሶ ጫፍ ይኖር እንደ ነበር ኢቫግሬዎስ የዐይን ምስክር ነው። ስምዖን ከማያምኑ አሕዛብ፣ ከሐሰተኛ መምህራንና ከአይሁድ ሃይማኖት መሪዎች ጋር ብዙ ጊዜ ውይይት ያደርግ ነበር። ብዛት ያላቸው አሕዛብና የዐረብ አርብቶ አደሮች በስምዖን ዘዓምድ በኩል ወደ ክርስትና ሕይወት ተመልሰዋል። /ዶ/ር ሥርግው ሐብለ ሥላሴ፤ የአማርኛ መዝገበ ቃላት፤ ገጽ 97-98/።

...#
ስምዖን ዘዓምድ በተጋድሎ ዘመኑ አይተኛም፤ አይቀመጥም ነበር። አብዝቶ ከመጾሙ የተነሣ ወገቡ በጣም ይተጣጠፍ ነበርና ጎንበስ ሲል እግሩን በጭንቀላቱ ይነካ ነበር። ከዕለታት በአንዲት ቀን 1244 ስግደት ሁሉን ቻይ ለሆነው አምላክ ሲሰግድ አንድ ሰው ተሰውሮ የስግደቱን ቁጥር ብዛት ይቆጥር ነበር። በመጨረሻ ግን መቁጠሩ ስለ ሰለቸው መቁጠሩን ተወው። ስምዖን ዘዓምድ ለሰውነቱ መሸፈኛ የሚሆን የአራዊት ቆዳ ይለብስ ነበር። በአንገቱ ዙሪያ ሰንሰለት ያደርግ ነበር። የጌታን ሥጋና ደም ሲቀበል እንኳን በዓምድ /ምሰሶ/ ላይ ቆሞ ነበር። /History of the Christian Church, volume III; Nicene and post – Nicene Christian. A.D. 311-600/.

የስምዖን ወላጆች ዘወትር ልጃቸውን ለማየት ይናፍቁ ነበር። አባቱ እግዚአብሔር ስላልፈቀደለት ስምዖን ዘዓምድን ሳያየው ሞተ። እናቱ ግን ልጇን ስምዖንን ለማየት ስለ ጓጓች፣ ስምዖን ያለበትን ቦታ ጠይቃ ከብዙ ዘመናት በኋላ ወደ እርሱ መጣች። ልጇ ስምዖን ድንጋይ ምሰሶው ላይ ቁሞ አገኘችው። አይታውም ስቅስቅ ብላ አለቀሰች፤ እግዚአብሔርንም አመሰገነች። ስምዖን ከቆመበት የድንጋይ ምሰሶው በታች ተኛች። ቅዱስ ስምዖንም ጌታችን አምላካችን መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ለእናቱ በጎ ነገርን ያደርግላት ዘንድ ስለርሷ ለመነ /ጸለየ/። ያን ጊዜም እናቱ ስምዖን ዘዓምድ በሚጸልይበት ምሰሶ ስር እንደ ተኛች ወይም በእንቅልፍ ላይ እንዳለች ዐረፈች። ከደንጊያው ምሰሶ በታችም ቀበሩዋት።

ለበጎ ነገር የማይተኛው ሰይጣን ስምዖን ዘዓምድን ለማሳት የማያደርገው ነገር አልነበረም። ሰይጣን በስምዖን ላይ ቀንቶ እግሩን መታው፤ ከእግሩ ትል እየወደቀ በአንዲት እግሩ ለብዙ ዓመታት ኖረ። ከዚህም በኋላ የሽፍቶች አለቃ ወደርሱ መጥቶ ንስሐ ገባ። ጥቂት ቀኖችም ኑሮ ዐረፈ፤ በጸሎቱም የዘለዓለም ሕይወትን ወረሰ። ወደርሱ ስለሚመጡ ብዙ ሰዎችም የውኃ ጥማት እንዳያስጨንቃቸው ወደ እግዚአብሔር ለምኖ ከድንጋይ ምሰሶው ስር ፈዋሽ ጠበል አፈለቀላቸው። የካቲት ዘጠኝ ቀን የሚነበበው ስንክሳር እንደ ሚተርከው የስምዖን ዘዓምድን ቅድስና በመንፈስ ቅዱስ መነጽርነት የተመለከተው አባ በርሱማ የተባለ አባት ነው።

አባ በርሶማ በኤፌሶን ንስጥሮስን ለማውገዝ ከተሰባሰቡት ሊቃውንት አንዱ ነበር። ስምዖን ዘዓምድን ሊያየው ወደደ። ስምዖንም የአባ በርሱማ ዜና ከብዙዎች ሰዎች ሰምቶ ነበር። አባ በርሶማ ወደ ስምዖን መጥቶ እርስ በርሳቸው በረከትን ተቀባበሉ። በኋላም በሶርያ አገር እያስተማረ በፊታቸው ተአምራትን በአደረገ ጊዜ በትምህርቱ ብዙዎች አመኑ። /ስንክሳር፣ ዘወርኀ የካቲት/። በኋላም ወደ ሌላ ምሰሶ ተዛወረ። በእርሱም ላይ እየተጋደለ ሠላሳ ዓመት ኖረ።

ስምዖን ዘዓምድ ብዙዎች አረማውያንንና ከሐድያንን አስተምሮ አሳምኖ ወደ ፈጣሪያቸው እግዚአብሔር መልሷቸዋል። ቅዱስ ስምዖን በዚያ ረጅምና አድካሚ ጉዞ /ተጋድሎ/ ቀናትን፣ ሳምንታትን፣ ወራትንና ዓመታትን ለሚያቃጥል ፀሐይ፣ ለሚያርስ ዝናም፣ ለሚሚጭር ጫካ /እሾህ/፣ ለሚያቈጭ ውሽንፍር ራሱን መሥዋዕት አድርጐ ገብሮ ለበርካታ ዓመታት ቆሟል። ዕለት ዕለት በሞት ጥላ ውስጥ እያለፈ በሰማዕትነት ኖሯል። በምድራዊ ቆይታውም ለሥጋዊ ምቾትና የነፍስ ዕረፍት ቦታ አልሰጠም። ከዚህ ይልቅ ለሌሎች ሰዎች ለላቀ የቅድስና ሕይወት ከልቡ ተጣጣረ እንጂ፣ በሰማይ ላለው የከበረ ሽልማት እና በምድር ላይ ለማይሞተው ስም ተጋደለ። ስምዖን ዘዓምድ በተወለደ በ69 ዓመቱ በ459 ዓ.ም ነሐሴ ሦስት ቀን በሰላም ዐርፎ ወደ ወደደው ክርስቶስ ሄደ፣ የዘላለም ሕይወትንም ወረሰ።

የአንጾኪያው ሊቀ ጳጳስ ቅዱስ አባ ስምዖን እንዳረፈ በሰማ ጊዜ ካህናትን ዲያቆናትንና የአገሩን መኳንንቶች ከእርሱ ጋር ይዞ የቅዱስ አባ ስምዖን ሥጋው ወዳለበት ደረሰ። በታላቅ ክብርም ተሸክመው እየዘመሩና እያመሰገኑ አድርሰው በቤተ ክርስቲያን ውስጥ አኖሩት። ከሥጋውም ድንቆችና ተአምራቶች ታላቅ ፈውስም ተገለጡ። የቅዱስ ስምዖን ልመናው ይደረግልን፤ በረከቱ ይደርብን። አሜን።

ወስብሐት ለእግዚአብሔር

ማኅበረ ቅዱሳን